# የአብዮት ውርሶች

## <u>መርገምትና ጸጋ</u>

ከገረመው ሃይሉ ( ካርቱም ሱዳን )

እኔ መቼም በግልጹ ላይ እንኳ ለምን እንደማንግባባ እንደደነቀኝ አለ። የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ከማይግባቡበት አንዱ አብዮት በተባለው በታሪካችን ትልቅ ቦታ በሚሰጠው ክስተት ላይ። እናም እኔ «አብዮታችንን» እንዴት እንደማየው ከሶስት አመታት በፊት ይህን አልኩ።

ለመሆኑ አብዮትም አንዳች የሚወረስና የሚወደስ ነገር አለውን ? ብላችሁ ብትጠይቁኝ እንዴታ ብዩ በኩራት እነግራችኋላውሁ :: ግን ደግሞ ውግዝ ከመ አርዮስ ብለን በአንድ ድምጽ አውግዘን የምንቀብራቸው እጅግ ብዙ አብዮት ወልድ መርገሞች ወይም ነቀርሳዎች አምጥቶብናል ብየም የእርግማኔን መአት እንደማወርድበትም አልደብቃችሁም :: እነዚህን የአብዮት መርገሞችንም ቀብረን የትንሳኤ ቀን እናውጅ ብየም ጥሪየን አቀርባለሁ ::
የመጣጥፌን ንኡስ አርእስት መርገምና ጸጋ ማለቴም ለዚህ ነው::

ወያኔን ለመጣል የተደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል እስከዛሬ ወደ ፊት አንዲት ጋት ፎቅ አለማለቱን ሁላችን አውቀናል :: ለዚህ ደግሞ የወያኔ ጥንካሬ ሳይሆን የራሳችን ድክመት መሆኑ የጋራ ግንዛቤችን ሆኗል። እናም መጀመሪያ እኛ በአሰራርም በአስተሳሰብም እንለወጥ ብለን እርስ በርሳችን እንዳችን አንዳችንን መስበክ ከጀመርን ቆይተናል :: እኔም ዛሬ በዚሁ ላይ አክላለሁና እነሆ !

የነገሬ አሃዱ የሚጀምረው ከድክመታችን አቢይ ምክንያቶች ጥቂቶቹ እነዚሁ የተጣቡን አብዮት ወለድ ወይም አብዮት አመጣሽ በሽታዎች ናቸው ብሎ ማስረገጥ ነው ::

በ1966 ዓ.ም. የተቀጣጠለው አብዮት የህዝብ ብሶት ውጤት ለመሆኑ አንድና ሁለት የለውም :: ያኔ አብዮት ለአገር እድገት ፥ለልማትና ብጽግና አቋራጭ መንገድ ነው ተብሎ በሁሉም ለውጥ ፈላጊ ሃይል መታመኑም እርግጥ ነው :: በመሆኑም የህዝብና የወገን ብሶት አንገብግቦት ስቃይ መካራውን ሊታደግ ታጥቆ በተሰለፈው ለውጥ ፈላጊ የህብረተሰብ ክፍል በተለይም በወጣቱ መታጀቡም እውነታ ነው ::

ዛሬ ወደኋላ መስለስ ብለን ስናይና የደረስንበት ስንማትር ያ የሃገርና የወገን ስቃይ፥ መከራና ግፍ ሞልቶ ሲፈስ የተንቀሳቀስው አብዮት ያው እናንተም እኔም በምናውቃቸው ባለአዋቂ ሹፌሮች ተዘውሮ

እንቁዎቻችንን ቅርጥፍጥፍ አድርጎ በልቶ ከአፍንጫቸው ስር ዘለው የማያስቡትን በቻ አስቀርቶልን ይኸው አገርም ህዝብም አሳር ፍዳቸው አሳልቅብሷል:: የተረፉ አንዳንድ አርቆ አሳቢዎች ቢኖርም የማይግባቡ ፥ የተበታተኑና በየቦታው የተዝረከረኩ በመሆናቸው በዚህ በኩል በውያኔና በጸረ- አንድነት ህይሎች በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉን አዋቂዎች አድርገው ራሳቸውን በሾሙ በጣም ጥቂት ሁሉን አክቾልቻዮች ጩኸት ተውጠውና ስሚ አጥተው ከወዲያ ወዲህ እየተሳጉ ትግሉን በሚፈልገው መልክ ፈቅ ማድረግ አልቻሉም ።

በመሆኑም ለአዲስ የህብረት ግንባታ ታጥቀን ስንነሳ የነበሩንን በጎ ጎኖች አጠናክረን እውቅና ሰጥተን ፥ ደካማና አፍራሽ እንዲሁም መርዘኛና አገር አጥፊ ከፋፋይና መርገምቶቻችንን ደግሞ ቀብረን ወይም ባንድ ድምጽ አውግዘን መሆን ይጠበቅብናል ባይ ነኝና የበኩሌን ትንሽ እላለሁ ::

ከአብዮቱ ጸጋዎች ብጀምርስ !

አዎ ከአብዮቱ ከወረሳቸው ድንቅና ውብ ባህሎች አንዱ ለአገር ፥ለወገን ሲሉ ባንድነት ፥ዘር ፥ጾታ ፥ ሙያ ፥ እድሜና ሃይማኖት ሳይውስናቸው ሁሉም ለለውጥ የቆሙ ኢትዮጵያውያን ባንድነት መቆማቸው ነው:: ባመኑበት ጎራ ተሰልፈው ባንድነት መሰዋታቸው ነው:: አማራው ፥ ኦሮሞው ፥ ትግሬው ፥ አገው ፥ ጉራጌው ፥ ወላይታው ፥ ሺናሻው ፥ ኩናማው ፥ቢለኑ፥ ሃዲያው ፥ ሲዳማው ፥ አፋሩ ፥ ጉሙዙ ፥ሱማሌው ፥ ሀደሬው ፥ ወዘተ ባንድነት ላመነበት የትግል ውሎ በዱር በከተማው ተሰልፈው ባንድ ላይ መስዋእትነት ከፍለዋል :: ላመኑበትም ባንድነት እስከወዲያኛው ተሰናብተዋል ::

አብዮት ብሄረሰቦች በቋንቋቸው፣ በባህላቸው እንዲኮሩ ያደረገ፤ የሃይማኖት እኩልነትን ያጎናጸፈ ለመሆኑ የሚከራከር የለም። ግፈኛውን የጭሰኝነትና ገባርነት ግኙነት አክትሞ መሬት ላራሹ መባሉ ትልቁ የአብዮት ፍሬ ነበር። ይህ የደርግ ስጦታ ሳይሆን የህዝባዊ አብዮት ወጤት ነበር። የያኔ አብዮተኞች እነዚህ ህዝባዊ ጥያቄዎች እንዲመለሱ ባመኑበት ጎራ ተሰልፈው ታግለዋል።

ዛሬ ወያኔና የውጭ ጠላቶች እንደተመኙት ኢትዮጵያ ያለመፈራረሷ ሚስጥር ያልገባቸው ካሉ ይኸው እነዚህ ምርጥ የኢትዮጵያ ልጆች ዘር ፥ ሃይማኖት፥ ጾታና እድሜ ሳይለዩ ያደረጉት ያንድነት ተጋድሎ አሻራ ውጤት ነው:: ይህ ድንቁ ልንከባከበው፥ ልናድሰው ፥ ልናበለጽገውም ፥ የሚገባን በዘመነ አብዮት ገነው ከወጡት ጸጋዎቻችን አንዱ ነው:: ይህ አዲስ የአብዮት ግኚት አይደለም :: አድዋና ማይጨው እንዲሁም የአምስቱ አመት የአርበኞነት ተጋድሎ ቅርስ አካል ናቸው:: ይሁንና እኩልነትን መስረት አድርጎ ልዩ ስፋትና ጥልቀት ያገኘው በዘመነ አብዮት ነው ማለት ከእውነት መራቅ አይሆንም :: ወያኔና ሌሎች ዘረኛና ገንጣይ

ሃይሎች የዘሩት መርዘኛ የጎጠኝነት እምነትን ከስሩ መንግለን የምንጥለውም በዚህ በህብረብሄራዊነት ጥላ ስር የተደረገውን ተጋድሎ ልዩ ቦታ ስንሰጠውን ስናበለጽገው ነው። ሌላ መንገድ የለም። ከዚሁ ጋር የሚያያዘው ደግሞ ሃብት ፥ንብረት፥ ቤትና ትዳር ይቅርብኝ ብለው ራሳቸውን ለህዝብና ላአገር ሰጥተው ላመኑበት ሙሉ ህይወታቸውን የሰጡ አያሌ ጀግኖችን ማፋራት ነው ። ይህም አዲስ አይደለም ግን የኢትዮጵያ ትንሳኤ እውን እስኪሆን ቃል ኪዳናቸውን ጠብቀውና አክብረው እጅግ ብዙዎች ከሰላሳ አመታት በላይ በጸናት ትግሉን መቀጠላቸው ልዩና አዲስ ጸጋችን ነው ።ይህ በአንድነቱ ጎራ የተሰለፉትን የየትኛኛውንም ድርጅት አባላት ይመለከታል። ሌሎች ሺህ ከሃዲዎች ጎጠኞችና ሆዳሞች ማፍራታችን ይህን አይለውጠውም።

ለእንደዚህ መሰሎች ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ምስረታ ፥ ለህግ የበላይነት ፥ ለአገር ሉአላዊነትና ብልጽግና እውን መሆን ሲሉ በየትኛውም ወገን ተሰልፈው መስዋትነት ለከፈሉ ውድና ድንቅ የኢትዮጵያ ልጆች ክብርና እውቅና ስንስጥ ለመጭው ትግልም ሰላማዊ አልነው ሁለገብ ትግል ግንባራቸውን የማያጥፉ ጀግኖችን እናፈራለን ። እኛ ያላደረግነውን ላደረጉ ደፋሮችና ትግሉን በመስዋትነታቸው ቀጥለው ላስረከቡን ኩሩ ዜጎች ተገቢ ቦታቸውን መስጠት የመጪው ትግላችን አንዱ መደላድል ነው።

ከዚህ በተቃራኒ ግን ከዚህ በፊት የተደረገውን ሁሉ ብናክቸለችለው መስረት የለሾች ከመምሰላችን ባሻገር ከእውነታው የራቅናን ገና ኢትዮጵያንና ችግሯን ያልተረዳንና ያልገባን ፥ መሆናችንን አመልካች ነው። ይህ ደግሞ እንደ ደርጉ ወይም እንደ ወያኔ ከአዲስና ከባዶ ጀምሮ አዲስ ታሪክ ለመጻፍ ያለን ከንቱ ምኞት ከመሆን አይዘልም። ያም የትም አያደርሰን ።

ሌላው አብዮት አጉልቶ ያወጣው የሴቶች ተሳትፎ ነው ። የኢትዮጵያ ሴቶች በተለይም ፊደል የቆጠሩት ወጣት ሴቶች ከአቻ ውንድሞቻቸው ጋር ላገራቸውና ለህዝባቸው ሲሉ ያስመዘገቡት ታላቅ ተጋድሎ በአይነቱም ሆነ በጥንካሬው በኢትዮጵያ ታሪክ ተወዳዳሪ ተፈልጎ አይገኝለትም ። አይቻለውን ችለው፥ የጾታ ልዩነቱና የባህል ተጽእኖው ሳይበግራቸው ትግሎን በእጅጉ ያገዙት ወጣት ሴቶች የትግሉ አንቀሳቃሽ ግማሽ ሞተሮች ነበሩ ። ያው አብዮታችን እንደለሎቹ አገሮች አብዮቶች ሁሉ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ጭካኔም አስተምሮናልና የጭካኔውና የክፋቱ መጠና ዱካ ሁሉንም አሸማቆ ዛሬ ሴቶች በትግሉ የሎሚ ሽታ ብቻ ሁነዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም። እናም የኢትዮጵጵያ የሴቶች ለመብታቸውና ለአገራቸው ብልጽግናና እድገት ሲሉ ያደረጉት አስተዋጽኦ ጅምር አንድ ድንቅ የአብዮት ቅርስ ነው ማለት ይቻላል። ነውም ። የኢትዮጵያ አብዮት የኢትዮጵያ ሴቶች ለፍትህ፥ለዴሞክርሲና ህዝባዊ ስርአትን ለማዋለድ በተደረገው ተጋድሎ ፥ የታግሎ አታጋይነት ጽናት ብቃታቸውን፥

ያስመሰከሩበት ነው ። ዛሬ ግን በትግሉ መስክ የሴቶች ተሳትፎ ንፋስ እንደሚያላግው የኩራዝ መብራት በጣም በሩቅ ሆኖ ጭል ጭል የሚል ብቻ ሆኗል። እናም የወደፊቱ ኢትዮጵያን የማዳኑ ትግል ፍሬማ የሚሆነው የሴት እህቶቻችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ክቡር ቦታውን ከያዘ ብቻ ነው ብሎ ለወንዱም ለሴት እህቶቻችንም ማስታወሱ ደግሞ ተገቢ ነው። ባንድ እጅ ማጨብጨብ አይቻልምና !

**ወደ አብዮት መርገሞች እንለፍ**

በሌላ በኩል ግን የኢትዮጵያ አብዮት ፍጅት ነው ፥ ትርምስ ነው ፥እልቂት ነው ። ከተማ ጫካውን በደም ያጠበ ትውስታው አሁን ድረስ ሰቀጣጭ ታሪካችን ነው። ጥቅል ውጤቱ ሲታይ ደግሞ አገርን ወደፊት ሳይሆን በበዙ እጅ ወደ ኋላ የነዳ ነው ። ከዚህም አልፎ በህዝባችን በተለይም በፖለቲከኞቻንና ፊደል በቆጠረው መሃል መርገመት ተብለው የሚቆጠሩ ባህሎችን ወይም የአብዮት በሽታዎችን አምጥቶችናል። ዘርቶብናል ። በክሎናል ።

**ጥቂቶቹን ብቻ እንጥቀስ !**

የመጨካከን ባህል ፥ የመጎዳዳት ባህል ፥ የመጠራጠር ባልህ ፥ ፥ የክህደት ባህል ፥ የማያውቁትን የመተቸት ባህል፥ መስሎ የመኖር ባህል ፥ ያልሆኑትን ሆኖ የመታየት ባህል፥ የልመና ባህል ፥ የመናናቅ ባህል፥ በራስ ያለመተማመን ባልህ፥ የውሸት ባህል ፥ የመዘራጠጥ ባህል፥ፊደል የቆጠረ ሁሉ ሁሉን አዋቂ ሆኖና መስሎ ያለምንም ገደብና ይሉኝታ በማያውቀው ሙያና የእውቅት ዘርፍ የመታበይ ልዩ ባህልም አዳብረናል። ወያኔ ሙስና የሚል ስም ያወጣለት የጉቦኝነት ና የስርቆት ባህል፥ ወዘተ አዳብረናል። አበልጽገናል ። በነዚህ ላይ ወያኔ ያመጣብንን ደግሞ አክሉበት።

ወገኖች ! እነዚህ ሁሉ ከይሲ ነገሮች በብዙ ፖለቲከኞቻችንና ፊደል በቆጠሩ ወገኖቻችን ላይ ሰፍረዋል ።
እነዚህ የአብዮት ውርሶት በአስራራችን ፥ በአስተሳሰባችን ፥ በእርስ በስር ግንኙነታችን ፥ በባህሪያችን ወዘተ ጭምር ላይ ተጽእኖ ያላቸውና ስር የሰደዱ እንደ እርኩስ መንፈስ የሚያሰቃዩና የተጣቡን በሽታዎች ናቸው። እናንተ ያሻችሁን ስም አውጡላቸው እኔ የአብዮት በሽታዎች ብያቸዋለሁ።መርገሞችና ነቀርሳዎች ብየም ጨምሬላቸዋለሁ።

እነዚህ ድሮ አልነበሩብንም ብየም አልስብካችሁም ። ነበሩብን ። ግን በጥቂቶች የተወሰኑና በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል የተወገዙ ፥በጸያፍነት የሚታዩ ነበሩ። አብዮት ግን እውቅናና ፥ ህጋዊነት ሰጣቸው ። አበለጸጋቸው ።አስፋፋቸው። ልዩነቱ ይህ ነው።
ወደ ዝርዝር ከገባሁ አጭር መጣጥፍ ሳይሆን ስለአብዮቱ የሚያወራ ወደል መጽሃፍ ይሆንብኛልና ወደ ዝርዝር አልገባም ።

በዚህም የተነሳ ድንቁርናን አስፋፍተን አገርን ላለችበት አብቅተናል። የራሳችንን አንቋሽን የስዎችን ባህል የማወደስና የማስፋፋት የጥፋት ተልእኮም ተውጥተናል ። የመጥፎ ነገሮች ምሳሌ የበጎ ነገሮች ደግሞ ድሃ ና የአለም ማሚጠጫ አድርገናታል ። ይህም ወጣቶቻችንን በመጪው ዘመን ላይ ተስፋ አስቆርጦ የአውሮጳና አሜሪካ ናፋቂ አድርገናቸዋል ። አሜሪካንና አውሮጳን መናፈቅ ድሮም የነበረ ቢሆንም እንደዚህኛው ዘመን ግን በአገር ተስፋ ከመቁረጥ የመጣ አልነበረም። ወጣቶቻችን ተስፋ በመቁርጣቸው የተነሳም በሲጋራ ፥ በጫት፥ በእጽ ፥ በዝሙትና በመጠጥ ሱሶችና ልማዶች ተጠቂ እንዲሆኑ አድርገናቸዋል ።

አዎ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማህበራዊ ፥ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ነጻነት መከበር በተደረገው ትንቅንቅ ሳቢያ የተቀጣጠለው አብዮት ፈር ስቶ ለአገር ሉአላዊነት መናጋት መሳሪያ መሆኑንም እየጎመዘዘን ቢሆን ለንቀበልው የሚገባ እውነታ ነው ። የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ፥ የህዝቡን ባህልና ታሪክ ያላገናዘበው የተውሶ ፍልስፍናችን ለዘረኞችና ለጎጠኞች መፈርጠምና ለአድህሮት ሃይላት ጠንክረው መውጣት ከዚያም አልፈው ስልጣን ለመያዝ አበቃቸውና በታላቅ ተጋድሎ የተመለስውን ሉዓላዊነት መልሶ አሳጣን ። ኤርትራን ወደእናት አገሯ ለመቀላቀ ትልቁን ሚና ስለተጫዎቱት የሃገር ፍቅር ጀግኖቻች ታሪክ ሳናውቅ ስለ የቻይናው ረጅሙ ጉዞና የቦልሸቪክ ፓርቲ ታሪኮችን የምናበልብል ጉደኞች ሆነንና ሳናውቅ የወያኔ ሻቢያን ታሪክ ድለዛን አገዝን ።

በመሆኑም አብዮታችን ያልነው የፍጅት ክስተት የተወስኑ ድንቅ የሚባሉ ተመክሮዎች እንዳስተማረን ሁሉ ከላይ የጠቀስናቸውና አያሌ ስፍር ቁጥር የሌላችው መጥፎ ባህሎችም አምጥቶብን ወደ ፊት ሳይሆን ወደ ኋላ ሽመጠጥን ። የአንድነት ህይሉ ትግል ወደ ፊት ያልገፋውም ከዚሁ አብዮት ከተባለው የታርካችን ክፍል በወረስናቸው አፍራሽ ልምዶችና ባህሎች ተጽእኖም የተነሳ ነው ብል የተሳሳትሁ አይመስለኝም ። ለለውጥ እንነሳ ካልን ደግሞ መጭፎውን ከጥሩው ለይተንና መርጠን ጥሩን አዳብረን መጥፎውን ቀብረን በጎውን ደግሞ ለመጭው ትግላችን መደላድልነት ስንጠቀምበት ብቻ ነው ።

የኛ አብዮት ድንቅና ውብ የሆኑትን በእድሜ ፥ በተመክሮ ፥ በጾታ ፥ በእውቀት ወዘተ ልዩነቶቻችን ላይ የተመስረቱ የመከባበር ባህላችንን በእጅጉ ሸርሽሮ አናግቶብናል ። የመቻቻል ባህል በፖለቲከኞቻችን ዘንድ ብቻ ሳይሆን ምሁር ብለን በምንጠራው የህበረትሰባችን ክፍል ጭምር ከነጭራሹ አዳክሞብናል ። በመሆኑም ከችግሮቻችን የመውጣት አሃዱም የሚጀምረውም ከነዚህ የአብዮት መርገመቶች ስንላቀቅ ነው ።

ከሁሉም ከሁሉም መዘንጋት የሌለበት አብዮት የት ይደርሳሉ የተባሉ ወጣት ምሁሮቻችን፥ ለጋና እምቡጥ ወጣቶቻችን በዚህም በዚያኛውም ጎራ

ያጣንበት ሲስታውሱት አስጨናቂውና አስፈሪው÷የታሪካችን ክፍል መሆኑ ነው ። ይህ የመጠፋፋት የአብዮት ባህል ላንዴም ለሁሌም ተወግዞ መቅረት ያለበት ነው የነገሬ ዚቅ ።

ከአብዮት ታሪካችን ዘግናኙ ደግሞ የፖለቲካ ባላንጣችንን ለማንበርከክ ስንል የጠተቀምንበት የጭካኔ ስራችን ነው ። ዘመነ አብዮት በዘመነ መሳፍንት ተፈጸሙ ተብለው ከምናውቃቸው እጅ ከመቁረጥና ቤት ዘግቶ በእሳት ከማቃጠል በተጨማሪ ጡት የመቁረጥ ÷ በስስ ብልት የመጫወት÷ አይን የማፍረጥ ÷ጥፍር በጉጠት የማውጣት ÷ በዘይት ገላን የመጥበስ÷ ጀርባን በእሳት የማጋየት ÷ከነህይወት መቅበርና ወደ ገደል መጣል ወዘተ ወዘተ አዳዲስ ጭካኔዎችን በአብዮት ዘመን ተምረናል። አስተምረናል።

ወገኖች ! እንለውጥ ስንል ከእነዚህና መስለ ወደ እንሰሳነት ዝቅ ካደረጉን ስብእናዎቻችን እንውጣ÷ ስብአዊነት እንላበስ ማለትም ነው። ይህን አውሬነት በውስጣችን ቀብረን በጎ ነገር ማሰብም መስራትም አንችልም። ይህ ሁላችንንም የሚመለከት ነው። አብዮት ግፍና ጭካኔ ያላስተማረው ወገን ካለ ጥቂት ነው ። ሁሉም ያደረገውን ለማድረጉ ማጠየቂያው ደግሞ ያው ወደ ኋላ የነዳንን አብዮት ወደ ፊት ያራመደ መስሎ ት ነው። የሚያሳዝነውም ይኸው የምንሰራውን ስራ ውጤት ቀድመን አለማወቅ ነው።

ሁሌም የምንመኘው የተቃዋሚዎች ህብረት ተፈጥሮ ዘላቂነት እንዲኖረው ካስፈልገ እነዚህ የአብዮት መርገሞችን ላንዴም ለሁሌም ስንቀብርና ጸጋዎቹን ደግሞ ለመጪው ትግላችን ስናውላቸው ነው ።በህብረት ምስረታ ወቅት ትልቅ ትኩረት ሊሰጠቸው ከሚገባቸው ነገሮችም ያለመተማመን ወይም እርስ በርስ የመጠራጠር በሽታችን ነው ።የህብረት ትግሉ ትልቁን የኋልዮች ጉዞ የሚጀምረውም ይህ እርስ በርስ ያለመተማመን በፖለቲከኞቻችን መሃል ሲከሰት መሆኑን ልብ ማለቱም አከፋም ።

እግዜር እናንተንም እኔንም ከነዚህ የአብዮት በሽታዎች ይሰውረን ያለብንንም በቸርነቱ ይፈውስን !
አገራችንንም በቃሽ ይበላት !
አሜን !